# አድር ባይ ምንደኛ

አቋም የሌላቸው ፣ የማይጨበጡ
የተቅበዘበዙ የትም ፣ የሚሮጡ
ከመጣው ጋር ሁሉ ፣ የሚያዘጠዝጡ
አሉ በየስፍራው ፣ ሞልተዋል መች ታጡ
ሃፍረት የሌላቸው ፣ የሰው አይን ያወጡ ።

በመጥፎ ምግባሩ ፣ ሁሌም የፊት መሪ
ሆዱ የሚገዛው ፣ ቁራሽ ፍርፋሪ
ባገሩ የሚሸፍጥ ፣ ለጠላት አዳሪ
ወገን የሚያደማ ፣ ቅጥረኛ አሳፋሪ
ዛሬም ነገም አለ ፣ እንክርዳድ ብጣሪ
ያለ የነበረ ነው ፣ ወደፊትም ኗሪ ።

አዲስ ነገር ዛሬ ፣ መቼ ተፈጠረ
ሺ ሹምባሽ ነበረ ፣ ለጠላት ያደረ
ስንት አድር ባይ አለ ፣ ወገኑን ያስበላ
ሚስጥር የሚያቀብል ፣ የጠላት ደላላ
የባንዳ ያድር ባይ ፣ ታሪክ መቼ ያልቃል
ይነገር ካልንማ ፣ አመት መች ይበቃል ?

አገርና ህዝብን ፣ ወገን የበደለ
ከወዲህ ከወዲያ ፣ እያውደለደለ
አቄልኩኝ እያለ ፣ እራሱን ያቄለ
ወገኑን ያስፈጀ ፣ ወሬ እያቀበለ
በሁለት ቢለዋ ፣ የሚመትርም አለ ።

ቅንቅን የጀርባ እከክ ፣ የሀገር ደመኛ
እቶስቱሶ አዳሪ ፣ ልክስክስ ምንደኛ
በልቶ የማይጠግብ ፣ የቀን ጅብ ቀበኛ
አሳፋሪ ፍጥረት ፣ ስንት አለ ቅጥረኛ
በደም የታጠበ ፣ ጨካኝ ወንጀለኛ ።

ማነው ለእንግሊዞች ፣ መንገዱን የመራ
እንድትወድቅ ያረገ ፣ መቅደላና ቋራ ?
እኮ ማን ቢመራ ፣ ማን በተባበረ
ጣሊያን ጦሩን ይዞ ፣ አድዋ የሰፈረ ?
ስንቱ ነው ማይጨው ላይ ፣ በባንዳ የወደቀው
በወንድሙ ካራ ፣ አንገቱ የታረደው?

ከምድር ከሰማይ ፣ እጅግ የገዘፈ
ወንጀል የፈጸመ ፣ ትውልድ የቀጠፈ
እንደ መርገምት ፣ ጨርቅ ቆሸሾ ያደፈ
የጠላት መለዮ ፣ ለብሶ የተሰለፈ
ስንቱን አንገት ቀላ ፣ ወንድሙን ሰየፈ ።

የጠላት መሳሪያ ፣ ለጥቅም ያደረ
በሆዱ የሚያሰላ ፣ ነዋይ ያፈቀረ
ከእንግዴ ልጁ ጋራ ፣ ወይ አልተቀበረ
ወይንም ከናቱ ሆድ ፣ ሽል ሆኖ አልቀረ
አገርና ህዝብን ፣ አለ እንዳስመረረ
አገር አለባንዳ ፣ ምንኛ  ባማረ ።

እንደ ጋን እንስራ ፣ በግራዋ ቢያጥቡት
ዘቅዝቀው ባፍ ጢሙ ፣ የወይራ እንጨት ቢያጥኑት ።
    አጎብዳጅ ሆድ አደር ፣ ሁሌም ታጥቦ አይጸዳ
    ሲሻለው ወላዋይ ፣ ሲያቀስሰው ባንዳ
    ክብርን የማያውቅ ፣ ወስላታ ወራዳ
    መንገዱ ጠማማ ፣ ሁል ጊዜ ወልጋዳ
    አድሜውን ይፈጃል ፣ አገር እንደጎዳ ።

አድር ባይ ምንደኛ ፣ ብኩን የባከነ
እንኳንስ ለሰው ልጅ ፣ ለምላክ ያልታመነ
በምድር በሰማይም ፣ ነፍሱ የተኮነነ
ዘላለም ይኖራል ፣ አገር እንደጎዳ ፣ ህዝብ እንዳሳዘነ ።

ታዛቢው ... March 21, 2012